# በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካኝነት በሚከናወን ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቡና ግብይት ላይ የሚከፈለውን ታክስ አፈፃፀም በሚመለከት የወጣ መመሪያ ቁጥር 26/2001

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀፅ 64 እንዲሁም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 117/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካኝነት በሚከናወን ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቡና ግብይት ላይ የሚከፈለውን ታክስ አፈፃፀም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 26/2001 » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የተጨማሪ እሴት ታክስ

1. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቡና ግብይትን በሚያስፈፅምበት ጊዜ በእያንዳንዱ ግብይት የሻጩንና የገዥውን ስምና አድራሻ፣ የተሸጠውን ቡና ዓይነት፣ ብዛትና ዋጋ፣ ሽያጩ የተከናወነበትን ዕለት እንዲሁም በግብይቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ልክ የሚያሳይ ሰነድ አዘጋጅቶ ለሻጩ፣ ለገዥው እና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ያስተላልፋል፡፡

2. ገዥው ግዢውን በፈፀመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካኝነት የገዛውን ቡና ወደ ውጭ መላኩን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

3. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት መመሪያ በተመለከተው መሠረት ገዥው የሚያቀርባቸውን ሰነዶች በመመርመር ግብይቱ በተፈፀመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሂሣቡን ስሌት ያከናውናል፡፡ በምርመራው ወደ ውጭ ሳይላክ የቀረ ቡና መኖሩ ከተረጋገጠ በዚሁ ምርት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ገዥው ከነወለዱ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

## 4. ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ስለሚቀረው ግብር (withholding tax)

1. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አማካኝነት ከሚከናወን ግብይት ጋር በተያያዘ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 53 መሠረት ሻጭ ላቀረበው ቡና ከሚከፈለው ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ለግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን ሊከፈል የሚገባውን 2% ግብር የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀንሶ በማስቀረት በየወሩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ያደርጋል፡፡

2. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ በዚህ ዓይነት ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ቀሪ የተደረገበትን ታክስ ከፋይ ስም፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የግብይቱን የገንዘብ መጠን የሚገልፅ መረጃ በየወሩ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ይልካል፡፡

## 5. የተሻረ መመሪያ

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ቡና ላይ ለሚከፈለው ተጨማሪ እሴት ታክስ በዋስትና ስለሚያዝ ቫውቸር በ22/5/95 በቁጥር አመ3/16/88/896 የተላለፈው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 6. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 7/2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሣሥ 6 ቀን 2001 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ

የገንዘብና የኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር